# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ

## የአዲስ አበባ ከተማ መንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ
## የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት አስተዳደር

**መመሪያ ቁጥር 45/2013**

የካቲት 2009 ዓ.ም

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 45/2013

## መግቢያ

በአዲስ አበባ ከተማ በስፋት ከሚስተዋሉ መጠነ-ሰፊ የትራንስፖርት አገልግሎት አቅርቦት ችግሮች መካከል አንዱና ዋነኛው፤ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ስፍራና አጠቃላይ የአሰራር ሂደት ነው፡፡ በትራንስፖርት ዘርፍ ትራንስፖርትና የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የማይነጣጠሉ መሰረታዊ የሆኑ ጉዳዮች ናቸው፡፡ የመንገድ ላይ እና ከመንገድ ውጪ ያሉ የመኪና ማቆሚያ ስፍራዎች እጥረትና የአስተዳደር ችግሮች በሰፊው የሚስተዋሉ ሲሆን ተጠቃሚዎችም ተሽከርካሪዎችን ለማቆም ከቦታ ቦታ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በትራፊክ ፍሰቱ ላይ ተጨማሪ አሉታዊ ተጽዕኖ በመፍጠር ያለውን ወቅታዊ የትራፊክ መጨናነቅ ችግር የበለጠ እንዲባባስ አድርጎታል፡፡

የከተማውን የትራፊክ ፍሰት ለማሳለጥና ተደራሽ ለማድረግ በከተማው አስተዳደር እየተከናወኑ ካሉ ተግባራት መካከል ደረጃውን የጠበቀና ለተጠቃሚዎች ምቹ የሆኑ የተሽከርካሪ ማቆሚያ /ፖርኪንግ/ መሰረተ ልማቶች መገንባትና ማስፋፋት አንዱ በመሆኑና የከተማው አስተዳደር በትልቅ ወጪ የተለያዩ የተሽከርካሪ ማቆሚያ እያለማ መሆኑ ይታወቃል፤

እነዚህ የለሙ እና በመልማት ላይ የሚገኙ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶች የታለመላቸውን ዓላማ ይመቱ ዘንድ የሚተዳደሩበትን ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በከተማችን ለሚገኙ ስራአጥ ወጣቶች የስራ እድል ከመፍጠር አንጻር ከተማው ውስጥ ያሉ ወጣቶችን በተሽከርካሪ ማቆምያ አስተዳደር ስራ ላይ በማሰማራት ስራውን በአግባቡና በሃላፊነት እንዲሰሩ ለማድረግ በማስቻል እረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ተብሎ በመታሰቡ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በአዋጅ ቁጥር 43/2007 አንቀፅ 47 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ይህንን በከተማዋ አስተዳደር ወጪ የተገነቡት የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት አስተዳደር መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### 1. አጭር ርእስ

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጪ የተገነቡ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት ለማስተዳደር የወጣ መመሪያ ቁጥር 45/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፤

1. "ተሽከርካሪ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጪ የተገነቡ የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚጠቀሙ/የሚገለገሉ ማንኛውም ዓይነት ተሽከርካሪ ማለት ነው፡፡
2. "የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጪ የተገነቡ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ሲሆኑ የመሬት ላይ ፣ የህንፃ ፣ የህንፃ ሥር እና ዘመናዊ በኤሌክትሪክ ተንቀሳቃሽ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ማለት ነው፡፡
3. "ማህበራት" ማለት በአስተዳደሩ ወጪ የተገነቡ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት ለማስተዳደር ከኤጀንሲው ጋር የሥራ ውል የገቡ ጥቃቅንና አነስተኛ ማህበራት ማለት ነው፡፡
4. "የውል ክፍያ" ማለት ማህበራት በውል መሰረት አገልግሎት ለሰጡበት የሚከፈል ክፍያ ማለት ነው፡፡
5. "የአገልግሎት ክፍያ" ማለት የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚጠቀሙ ተገልጋዮች የሚከፍሎት ክፍያ ማለት ነው፡፡
6. "ኤጀንሲ" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ ትራፊክ ማኔጅመንት ኤጀንሲ ማለት ነው፡፡
7. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የመንገድ እና ትራንስፖርት ቢሮ ማለት ነው፡፡
8. "ከተማ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ ማለት ነው፡፡
9. "አስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ማለት ነው፡፡
10. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
11. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው ሴትንም ይጨምራል፡፡

### 3. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በከተማው ውስጥ በአስተዳደሩ ወጪ በተገነቡና በሚገነቡ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት እና መሰረተ ልማቱን የማስተዳደር አገልግሎት የሚሰጡ ማህበራት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

City Government of Addis Ababa Road and Transport Bureau

## ክፍል ሁለት

## የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት አስተዳደራዊ አወቃቀር እና ዓይነቶች

### 4. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት አስተዳደራዊ አወቃቀር

1. ኤጀንሲው በአስተዳደሩ የተገነቡትን የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት በመደበኛነት የኦፐሬሽናል ስራ የሚያከናውኑለት ማህበራት ጋር ቢበዛ ለሁለት አመት ውል በመፈጸም እንዲተዳደር ያደርጋል፡፡
2. ኤጀንሲው የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚያስተዳድሩ ማህበራት መረጣ ሲያከናውን፣ ከጥቃቅንና አነስተኛ ቢሮ የተደራጁ ከ 3 ያላነሱ ማህበራትን በደብዳቤ ለውድድር ይጋብዛል፡፡
3. ለውድድር ከቀረቡ 3 ማህበራት መካከል በሚያቀርቡት የዋጋ አዋጭነት መሰረት አንዱን በመምረጥ ወደ ስራ ያስገባል፡፡
4. ኤጀንሲው በአስተዳደሩ የተገነቡትን የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት ለማስተዳደር አመቺነት እንደየአስፈላጊነቱ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ወይም የስራ ክፍል በዚህ መመሪያ መሰረት ስራውን ተፈጻሚ ያደርጋል፡፡

### 5. ማህበራት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች

1. ማህበራት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

   ሀ. የተሽከርካሪ ጥበቃ አገልግሎት፤

   ለ. የአገልግሎት ክፍያ መሰብሰብ፤

   ሐ. የማቆሚያ ቦታውን ጽዳት እና የውበት ተግባራት፤

   መ. የእጥበት ቦታ ባለባቸው የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች የተሽከርካሪ እጥበት አገልግሎት፤

### 6. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት ዓይነት

1. ከቴክኖሎጂ፣ ከግንባታ ወጪ እና ከአገልግሎት አሰጣጥ አንጻር የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት በሚከተሉት ዓይነቶች ይመደባሉ፡፡

   ዓይነት አንድ፡- ዘመናዊ በኤሌክትሪክ ተንቀሳቃሽ የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት፤

   ዓይነት ሁለት፡- የህንጻ ወይም የህንጻ ሥር ተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት፤

   ዓይነት ሶስት፡- የመሬት ላይ ተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተልማት፤

### 7. የማህበራት የሰው ሀይል አደረጃጀት

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት የሚያስተዳድሩ ማህበራት ቢያንስ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 ስር የተመለከቱትን የሰው ሃይል ማካተት ይኖርባቸዋል፤
2. የማህበሩ አስተባባሪ ቢያንስ ዲፕሎማ እና ከዚያ በላይ የትምህርት ደረጃ ያለው ቢሆን ይመረጣል፤

City Government of Addis Ababa Road and Transport Bureau

## ክፍል አራት
## ተግባርና ኃላፊነት

### 8. የኤጀንሲው ተግባርና ኃላፊነት፡-

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቶችን በበላይነት ያስተዳድራል፤
2. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት ብቁ መሆኑን አረጋግጦ የብቃት ማረጋገጫ ይሰጣል፤
3. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት የመድን ሽፋን እንዲኖረው ያደርጋል፤
4. የተሽከርካሪ ማቆሚያ የአገልግሎት ዋጋ ተመን ያዘጋጃል፣ በየወቅቱ የሚኖረውን የገበያ ዋጋ እያጠና ያሻሽላል፤
5. ማህበራት ተግባራቸው በውሉ መሠረት እየፈፀሙ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ውሉን ጥሰው ሲገኙም በውሉ እና በዚህ መመሪያ መሠረት ተገቢ እርምጃ ይወስዳል፤
6. ለማህበራት በውሉ መሠረት የውል ክፍያ ይፈጽማል፤
7. ተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱ ክትትል ያደርጋል ብልሽት ሲያጋጥም ይጠግናል፤ ከጥገና በለሙያ አቅም በላይ ሲሆን የጥገና ስራ የሚሰራ ድርጅት ጋር በመዋዋል እንዲጠገን ያደርጋል፤ ሆኖም ችግሩ ከማህበሩ የአጠቃቀም እንዝላልነት የመጣ ከሆነ ወጪውን ማህበሩ እንዲሸፍን ይደረጋል፤
8. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱን የጥበቃ ስራ ይሰራል፤
9. ለማህበሩ አባላት መሰረታዊ የአስተዳደር አገልግሎት ስልጠና ይሰጣል፤

### 9. የማህበራት ተግባርና ኃላፊነት

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱን ይረከባል፣ በአግባቡ እና በጥንቃቄ አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤
2. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱ ውስጥ የሚገኙትንና የሚገለገሉበትን ይከታተላል፤ ጥበቃ ያደርጋል እንዲሁም ከሌሎች የጸጥታ አካላት ጋር የስራ ግንኙነት ያደርጋል፤
3. የተሽከርካሪ ማቆሚያ የአገልግሎት ክፍያ በቴክኖሎጂ የተደገፈ እና በመንግስት የክፍያ አሰራር ስርዓት መሰረት ይሰበስባል፤
4. በየቀኑ የተሰበሰበውን የአገልግሎት ክፍያ በውሉ መሰረት የሚጠበቅበትን ሂሳብ ወደ ኤጀንሲው የባንክ ቁጥር ገቢ ያደርጋል፣ በእሁድና በሌሎች የባዕላት ቀናት ባንኩ ዝግ በሚሆኑበት ጊዜ በሚቀጥለው የስራ ቀን ገቢ ያደርጋል፤
5. የባንክ ገቢ ደረሰኝ ከገቢ በኋላ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያደርጋል፤
6. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት ጽዳት እና ውበት የመጠበቅ ተግባራት ያከናውናል፤
7. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በተሽከርካሪያቸው ውስጥ የሚገኝ ማንኛውም ንብረት ከስርቆት ለመጠበቅ እንዲቻል እንዲያስመዘግቡ በማስታወቂያ የማሳወቅ ግዴታ ይኖርበታል፤
8. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማቱን በውሉ መሰረት በአግባቡ ማስተዳደር በሚችሉ የተለያየ ብቃት ባላቸው ሙያተኞች የተደራጀ እንዲሆን ያደርጋል፤
9. የገቢና የወጪ ደረሰኞች እንዲሁም አስፈላጊ ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፣ ሪፖርት ያደርጋል፤
10. ኤጀንሲው በሚያዘጋጀው ቅጽ መሠረት የአገልግሎቱን ክንውን በየሳምንቱ ሪፖርት ያቀርባል፤
11. ከተጠቃሚው የአገልግሎት እርካታ መረጃ በመሰብሰብ ተገልጋዩን ለማርካት የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራሩን ያሻሽላል፤
12. በሀላፊነት የተረከቧቸውን ንብረቶች በማንዋል እና በአጠቃቀም መመሪያ መሰረት መጠቀም ይጠበቅባቸዋል፤
13. በሀላፊነት የተረከባቸውን ንብረቶች ሲበላሹ ለኤጀንሲው ማሳወቅ ይጠበቅበታል፤



Government of Addis Ababa Road and Transport Bureau

14. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት የሚያስፈልጉ ልዩ ልዩ ክፍያዎች ማለትም የኤሌክትሪክ፣ የውሀ፣ እና የስልክ ወጪዎች ይከፍላል፤
15. በተሽከርካሪ ማቆሚያ መሠረተ ልማት ላይ የሚከናወኑ የማስታወቂያ ስራዎች ከኤጀንሲው ጋር በሚገባው ውል መሰረት ገቢ ያደርጋል፤
16. የማስታወቅያ ስራ ሲያከናውን ከኤጀንሲው ጋር በቅድሚያ ስምምነት መድረስ ይጠበቅበታል፤
17. አጠቃላይ የማስታወቂያ ስራዎች አፈጻጸም በተመለከተ በስራ ላይ የሚገኙ መመሪያዎችን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤
18. በተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታዎች የተሽከርካሪ እጥበት አገልግሎት ካለ ከኤጀንሲው ጋር በሚገባው ውል መሰረት አገልግሎት ይሰጣል፤
19. ለተሽከርካሪ እጥበት የሚውለውን የውሃና የኤሌክትሪክ ፍጆታ ማህበሩ ይሸፍናል፤

# ክፍል አምስት

# የተሽከርካሪ ማቆሚያ መስረተ ልማት የአገልግሎት ደረጃዎች፣ የአገልግሎት ክፍያ እና የውል ክፍያ

## 10. የአገልግሎት ደረጃዎች

1. ኤጀንሲው የአካባቢውን የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሽከርካሪ ማቆሚያ የአገልግሎት ደረጃዎች በሚከተለው ሁኔታ ይመድባል፡፡

   ደረጃ-1፡- በጣም ከፍተኛ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍላጎት ያለበት፤

   ደረጃ-2፡- ከፍተኛ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍላጎት ያለበት፤

   ደረጃ-3፡- መካከለኛ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ፍላጎት ያለበት፤፤

## 11. የአገልግሎት ክፍያ ተመን፡-

1. ኤጀንሲው የአገልግሎት ደረጃዎች መሰረት ያደረገ የአገልግሎት ክፍያ ተመን በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ ባለው ሰንጠረዥ መሰረት ይሆናል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም የአገልግሎት ክፍያ ተመኑን ኤጀንሲው ሊያሻሽለውና ሊከልሰው ይችላል፡፡

| ደረጃ | ተሽከርካሪው የቆመበት ጊዜ (በሰዓት) | በየ 1 ሰዓት የሚጨምር የክፍያ ተመን (በብር) | ማብራርያ |
|---|---|---|---|
| ደረጃ-1 | እስከ 1 ሰዓት | 6 ብር | መነሻ |
| | ከ 1 ሰዓት በላይ ሲቆይ | በየሰዓቱ 9 ብር | የመጀመሪያው ሰዓት በ 6 ብር ሲሆን የሚቀጥሉት ሰዓቶች በ 9 ብር ይታሰባሉ |
| ደረጃ-2 | እስከ 1 ሰዓት | 6 ብር | መነሻ |
| | ከ 1 ሰዓት በላይ ሲቆይ | በየሰዓቱ 7.5 ብር | የመጀመሪያው ሰዓት በ 6 ብር ሲሆን የሚቀጥሉት ሰዓቶች በ 7.5 ብር ይታሰባሉ |
| ደረጃ-3 | እስከ 1 ሰዓት | 5 ብር | መነሻ |
| | ከ 1 ሰዓት በላይ ሲቆይ | በየሰዓቱ 6 ብር | የመጀመሪያው ሰዓት በ 5 ብር ሲሆን የሚቀጥሉት ሰዓቶች በ 6 ብር ይታሰባሉ |

## 12. የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚያስተዳድሩ ማህበራት የውል ክፍያ

1. ማህበራት በሚሰጡት አገልግሎት መሰረት በፐርሰንት የሚሰላ የኮሚሽን አከፋፈል ስርዓት ይኖራቸዋል፡፡
   ሀ. ከተሽከርካሪ ማቆምያ አገልግሎት ከፍተኛው ጣርያ 30 ፐርሰንት ይሆናል፤
   ለ. ከተሽከርካሪ እጥበት አገልግሎት ከፍተኛው ጣርያ 20 ፐርሰንት ይሆናል፤
   ሐ. ከማስታወቅያ ስራ ከፍተኛው ጣርያ 5 ፐርሰንት ይሆናል፤

2. ኤጀንሲው ያሉትን ነባራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚያስተዳድሩ ማህበራት የአገልግሎት ክፍያን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ክትትል እና ቁጥጥር

## 13. ክትትል እና ቁጥጥር

1. ማህበራት የሚሰጡትን አገልግሎት በውሉ እና በመመሪያ መሰረት ስለመሆኑ ኤጀንሲው የክትትል እና የቁጥጥር ስራ ያከናውናል፡፡ ይህ ክትትል እና ቁጥጥር ስራ በሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ትኩረት ይሰጣል፡፡
   ሀ. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት ደህንነት እና በአግባቡ ጥቅም ላይ እየዋለ መሆኑን፤
   ለ. ማህበራት በውሉ መሰረት አስፈላጊውን የሰው ሀይል ማሰማራቱን፤
   ሐ. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት በሰዓቱ ለህብረተሰቡ ክፍት መሆኑን፤
   መ. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የክፍያ ስርዓቱን በተገቢው ሁኔታ ማከናወኑ፤
   ሠ. የጥበቃ አገልግሎት በበቂ ሁኔታ መኖሩን፤
   ረ. የማህበራት የአሰራር ስርዓት ለብልሹ አሰራር ክፍተት የሌለው መሆኑን፤
2. ኤጀንሲው የሚከተላቸው የክትትል እና ቁጥጥር ሂደት በሚከተሉት ጉዳዮች መሰረት ላይ ይሆናል፤
   ሀ. የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚያስተዳድሩ ማህበራት በሚያቀርቡት ሪፖርት፤
   ለ. የመደበኛ እና የድንገተኛ የክትትል ስራ፤
   ሐ. ተገልጋይ በሚያቀርበው ቅሬታ መነሻነት በሚያከናውነው ማጣራት፤
   መ. የተገልጋይ ዕርካታ ጥናት፤
   ሠ. የግምገማ ስራ በማከናወን፤

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ
City Government of Addis Ababa Road and Transport Bureau

# ክፍል ሰባት
# የጥፋት ደረጃዎች እና ቅጣት

## 14. የጥፋት ደረጃዎች፡-

1. ማህበራት የሚከተሉትን ጥፋቶች ፈፅመው ሲገኙ፤ በሚከተሉት ደረጃዎች የሚቀመጡ ሲሆን ለጥፋቱ የሚከናወነው ቅጣት በዚህ መመርያ አንቀፅ 14 መሰረት ይሆናል፡፡

ሀ. ደረጃ አንድ ጥፋት፡-

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የሚሰጥበት ሰዓት አለማክበር፤
2. ከተሽከርካሪ ማቆሚያው አቅም በላይ ተሽከርካሪዎች እንዲቆሙ ማድረግ፤
3. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በአግባቡ አለማስተናገድ፤
4. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች በቅደም ተከተል አለማስተናገድ፤
5. የተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት ተጠቃሚዎች የክፍያ መልስ አለመስጠት፤

ለ. ደረጃ ሁለት ጥፋት፡-

1. ከታሪፍ በላይ ሂሳብ ማስከፈል፤
2. የመሰረተ ልማት ጽዳት እና ውበት በአግባቡ አለመያዝ፤
3. የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ እያለ ሞልቷል ብሎ አገልግሎት መከልከል፤
4. ለኤጀንሲው መረጃ አለመስጠት፤
5. የአገልግሎት ክፍያ ታሪፍ መደበቅ፤
6. ሪፖርት በጊዜው አለማቅረብ፤
7. የውሸት ሪፖርት ማቅረብ፤
8. ያለፍቃድ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታን ለሌላ ተግባር ማዋል፣
9. ያልተፈቀዱ ማስታወቂያዎች መለጠፍ እና ማስለጠፍ፣
10. የውሃና ኤሌክትሪክ መስመሮችን እንዲሁም ሌሎች አገልግሎቶች በአግባቡ ያለመያዝ፤
11. የማይመለከታቸው ሰዎችን መሰብሰብ፤
12. የደንብ ልብስ አለመልበስ፤
13. ከማህበሩ አባላት ውጭ ስራ ማሰራት፤

ሐ. ደረጃ ሶስት ጥፋት፡-

1. የተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማቱ ላይ ሆን ብሎ ጉዳት ማድረስ፤
2. ያለአግባብ ብር ለማግኘት የክፍያ ማሽን ማበላሸት ወይም የተሳሳተ ክፍያ እንዲመጣ ማስደረግ፤
3. ለተሽከርካሪ ማቆሚያ አገልግሎት የተረከበውን መሰረተ ልማት እና ቁሳቁሶች ከዓላማው ውጭ ለማንኛውም የንግድ ስራ ወይም ለሌላ ተግባር ማዋል፤
4. ማህበሩ የተሰጠውን የአገልግሎት ስራ ለ3ኛ ወገን ቢያከራይ ወይም አሳልፎ ቢሰጥ፤
5. ከተሽከርካሪ ማቆሚያ ቦታ ውጪ ባሉ ቦታዎች የአገልግሎት ስራ መስራት፤
6. የተሽከርካሪ አካላት እና በውስጡ የተቀመጡ ንብረቶች መሰረቅ፤
7. የአገልግሎት ክፍያ ወደ ኤጀንሲው አካውንት በወቅቱ አለማስገባት፤

8. ያለደረሰኝ ሂሳብ ማስከፈል፤
9. ተቀጣጣይ ነገሮች መጠቀም፤

2. ሌሎች በዚህ መመሪያ ያልተጠቀሱ ጥፋቶች በኤጀንሲው በሚሰጠው ውሳኔ ከሶስቱም ደረጃዎች አንዱ ላይ ሊያርፍ ይችላል::

## 15. ቅጣት

1. ማህበራት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 14 ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ፈጽመው ሲገኙ ከታች በተገለጸው መሰረት ይቀጣሉ፤

| የጥፋት ዓይነት | ቅጣት | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመጀመርያ ጥፋት | የሁለተኛ ጥፋት | የሶስተኛ ጥፋት | የአራተኛ ጥፋት | የአምስተኛ ጥፋት | |
| ደረጃ -1 | የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ | 1,000.00ብር | 5,000.00ብር | 10,000.00ብር | ውል ማቋረጥ | በጥፋት ምክንያት ለሚከሰቱ የንብረት መበላሸትና መጉደል እንዲሁም የገንዘብ ኪሳራዎች ተሰልቶ እንዲከፈል በማድረግ እና በሰንጠረዥ የተገለጹትን ቅጣቶች ይቀጣል:: |
| ደረጃ -2 | 1,000.00ብር | 5,000.00ብር | 10,000.00ብር | ውል ማቋረጥ | | |
| ደረጃ -3 | 10,000.00ብር | ውል ማቋረጥ | | | | |

2. በአንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 ላይ የተገለፁት የቅጣት ክፍያዎች ከሚከፈለው የአገልግሎት ክፍያ ይቀነሳል፤
3. በአንቀፅ 14 በደረጃ ሶስት ላይ የተገለፁት የጥፋት ዓይነቶች ሲፈፅም ቢገኝ በአንቀፅ 14 ንዑስ አንቀፅ 1 በተገለፀው መሰረት ቅጣቱ እንዳለ ሆኖ በህግ የሚያስጠይቅ ከሆነ ተጠያቂ ይሆናል::
4. በተለያዩ ሁኔታዎች ችግሮች ሲፈጠሩ ኤጀንሲው የራሱ የሂሳብ ሠራተኛ በመመደብ ክፍያዎችን ሊሰበስብ ይችላል::

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 16. ስርቆት

በተሽከርካሪ ማቆሚያ መሰረተ ልማት፣ የማቆሚያ አገልግሎት በሚያገኙ ተሽከርካሪዎች እንዲሁም በሀላፊነት ከተገልጋዮች በተረከቧቸው ንብረቶች ላይ የስርቆት ተግባር ቢያጋጥም ድርጊቱን የፈጸመ አካል በወንጀል ህግ ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበሩ በአንቀፅ 14 መሰረት ይቀጣል፡፡

### 17. ስለመቋረጥ

ማህበሩ ወይም ኤጀንሲው በአንቀጽ 14 ላይ የተጠቀሱትን ጥፋቶች ውጪ በውሉ መሰረት ስራውን መቀጠል የማይቻልበት ሁኔታ ደርሰዋል ብሎ በሚያምንበት ወቅት የስራ ውሉን ለማቋረጥ ማህበሩ ወይም ኤጀንሲው ሶስት ወር አስቀድሞ ማሳወቅ ይጠበቅበታል፤

### 18. የመተባበር ግዴታ

1. ማንኛውም የተሽከርካሪ ማቆሚያ የሚያስተዳድር ማህበርም ሆነ የሚመለከተው አካል ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ ይጠበቅበታል፤
2. ማህበሩ ተሽከርካሪዎች ከተሰራው መሰረተ ልማት ውጪ ባለው አካባቢዎች እንዳይቆሙ ይጠብቃል፡፡ ቆመው ከተገኙ ለሚመለከተው የህግ አካል ያሳውቃል፡፡ ሆኖም ተሽከርካሪዎች ቆመው ቢገኙ ማህበሩ በአንቀፅ 14 ላይ በተቀመጠው በደረጃ 1 ቅጣት ይቀጣል፤ ይህ የሚሆነው ለህግ አካላት ማሳወቃቸው ማረጋገጫ ማቅረብ ካልቻሉ ብቻ ነው፡፡

### 19. ተፈጻሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎች

ይህንን መመሪያ የሚቃረኑ ማንኛውም መመሪያዎች እና ልማዳዊ አሰራሮች በዚህ መመሪያ ላይ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም ፡፡

### 20. መመሪያን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ እንዲሻሻል ባስፈለገ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድ እና ትራንስፖርት ቢሮ ሊሻሻል ይችላል፡፡

### 21. መመሪያው ተፈፃሚ የሚሆንበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮ ኃላፊ ተፈርሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ ሆኗል፡፡

የካቲት 2009 ዓ.ም

ሰለሞን ኪዳኔ (ዶ/ር ኢንጂነር)

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ